# ከሱዳን እስከ ሰርቢያ-- የሀበሻ ፖለቲከኞች ምን ይማራሉ? (ክፍል 2)

ከገመቹ ተካልኝ

በሱዳን ያለው የኦማር በሺር አምባገነናዊ አገዛዝ መጪውን ምርጫ ለማጭበርበር በመነሳቱ ዋናው ተቃዋሚ ማለትም የደቡብ ሱዳን ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር በምርጫ አልሳተፍም ብሎ ወስነ። ሌሎች ድርጅቶችም እንሳተፍም እንዲሉ ጥሪ አስተላልፏል። በሺርም በምርጫ ካልገባችሁ በመጪው ዓመት መጀመሪያ ላይ የሚደረገውን የደቡብ ሱዳን ውሳኔ ሕዝብ አስተላልፋልሁ ብሎ አስፈራርቷል። በሃገራችን ወያኔ ምርጫውን ለማጭበርበር ዝግጅቱን መጨረሱ በሁሉም የታውቀ ነው-- ተገቢውን እምቢታ ማሰማት ወይም ማዕቀብ ማድረግ ያቃተው ታዲያ ለምንድን ነው?

ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅን በተመለከተ ደግሞ ከዓመታት በፊት በቀድሞይቷ ዩጎዝላቪያ ተፈጸመ ለተባለ ፍጅት የሰርቢያ መንግስት ይቅርታ በይፋ ጠይቋል። ይህም ለዕርቅና ሰላም ወሳኝ ነው ተብሎ እንደነበር የሚታወስ ነው። በግፍ የፈሰሰ ደም ይጮሃልናም ነው። መቸ ነው የእኛ ፖለቲከኞች --ያውም ታጋይ በሉን ሊሉ የከጀሉት-- ከሕዝብ ይቅርታን የሚጠይቁት? ይነስ ይብዛም መቼ ነው የዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ድፍረት የሚኖራችው? እነ ስዬና ገብሩ መቼ ነው ከመለስ ጋር ሆነን ለፈጸምነው ይቅር በሉን የሚሉት? መቼ ነው እነ ኦነግ ለአሶሳ ፍጅት ፤ ለበደኖ ፍጅት  ሕዝብን ይቅርታ የሚጠይቁት? መቼ ነው ወያኔ የኛው ቢቀር የሶማሊያን ሕዝብ ይቅር በለኝ የሚለው?

ከዚህ በተያያዘ ደግሞ መቸ ነው የሓበሻ ፖለቲከኞች በሃገራችን አርአያ መሆን የሚችሉ ጀግኖች የጠፉ ይመስል የባዕዳንን ስም መጥራት የሚያቆሙት? ዓመት የታሰረውን ማንዴላ ማለቱ መቼ ያበቃል?

ለብርቱካንስ አምሳያ የሚሆኑ የሃገራችን ሴት ጀግኖች ጠፍተው ነው በርማ ድረስ የሚኬደው? ከ1997 በፊት አንድ ከሃዲ ማንዴላ ተብሎ የነበረውስ ይረሳል? ከተስተካከለስ ብርቱካንን ጀግና እንደ ሸዋረገድ፤ እንደነ አበራሽ ወዘተ ማለቱ አይሻልም? በትንሹም ቢሆን ራሳችንን ለማክበር ከፈለግን ማለት ነው።

በወያኔ ምርጫ ላይ ማዕቀብ !!
ሕዝብን የበደሉና ይቅርታ ያልጠየቁ ከሕዝብ ጎራ ሊገቡ አይችሉም !!!

**Source: Reuters**
**KHARTOUM, March 31 (Reuters) - South Sudan's leading party said on Wednesday it was withdrawing its candidate for the presidency in next month's election.**
**"We decided that Yasir (Arman) should end his campaign for the presidency of the republic," the Sudan People's Liberation Movement (SPLM) vice-chairman Riek Machar told reporters.**
**Machar cited the conflict in Darfur and electoral irregularities, adding the party would also boycott all levels of elections in Darfur. (reporting by Opheera McDoom, writing by Andrew Heavens)**

March 31, 2010
**Serbia's parliament approved a declaration Tuesday condemning the 1995 Serb massacre of 8,000 Muslims in Srebrenica, in a bid to distance the country from past warmongering under the late strongman Slobodan Milosevic.**

**The declaration passed with a slim majority of 127 votes in the 250-seat parliament, after a daylong debate that underscored persisting divisions in the country over Serbia's role in the 1990s conflict.**

**"The National Assembly of Serbia harshly condemns the crime committed against the Bosnian residents of Srebrenica in July 1995 ... expressing condolences and apology to the victims' families because not all was done to prevent this tragedy," the declaration says.**

**Serb President Boris Tadic called the resolution "historic."**